OFFICE OF THE STATE
SUPERINTENDENT OF EDUCATION

ውድ ወላጅ ወይም አሳዳጊ፣

በፀደይ 2023፣ ልጅዎ የDCን የሳይንስ ምዘና ወስዷል/ወስዳለች። የDC ሳይንስ ምዘና ለተማሪዎች በጣም አስፈላጊ የሆኑትን ሳይንስ ላይ መተማመን እና ስኬት ወደሚመሩ እንደ ሳይንሳዊ አስተሳሰብ፣ ችግር መፍታት እና ስሜትን የማሳደግ ችሎታ የመሳሰሉ የሳይንስ ዕውቀት እና ክህሎቶችን የሚለካ ነው።

የኮሮናቫይረስ (ኮቪድ-19) ወረርሽኝ በመማር ማስተማር እና በተማሪዎች መማር ላይ ተፅእኖ ያደረጉ ተግዳሮቶችን እንዳመጣ እናውቃለን። እንደ ወረዳ፣ የዘንድሮው ዓመት የምዘና ውጤቶ ካለፈው አመት ጋር ሲነጻጸር መሻሻል መኖሩን አሳይተዋል፣ ይህም በየእለቱ በት/ቤቶች እየተካሄደ ያለውን ጠንካራ ስራ ያሳያል። የስቴት አቀፍ ምዘና ውጤቶች በዲስትሪክቱ ዙሪያ ያለውን የተማሪ አፈጻጸም ለመመልከት ጠቃሚ የመረጃ ምንጭ ሆነው ይቀጥላሉ፣ እና ተማሪዎቻቸውን እና አስተማሪዎቻቸውን እንዴት በተሻለ ሁኔታ መደገፍ እንደሚችሉ የት/ቤቶችን ውሳኔ ለማሳወቅ ይጠቅማል።

ልጅዎ ላጠናቀቀው የDC የሳይንስ ምዘና ከልጅዎ ትምህርት ቤት የውጤት ዘገባ ይደርሶታል። ይህ መመሪያ ከልጅዎ የውጤት ዘገባ ሊማሯቸው ወደሚችሏቸው ጠቃሚ የግንዛቤ ነጥቦች በመምራት ልጅዎ በቀጣዩ አመት እንዲሻሻል ለመርዳትም ግብዓቶችን ይሰጥዎታል። የልጅዎ የውጤት ሪፖርት ካልደረሰዎት፣ እባክዎ በ2022-23 የትምህርት ዘመን ልጅዎ የተማረበትን/የተማረችበትን ትምህርት ቤት ያነጋግሩ እና ለቅጂው ይጠይቁ።

የልጅዎ የDC የሳይንስ ምዘና ውጤት ዘገባ ልጅዎ በጥሩ ሁኔታ የሚሰራባቸውን ወይም ተጨማሪ ድጋፍ የሚፈልግባቸውን ቦታዎች ለማንፀባረቅ አፈፃፀምን ግልፅ ያደርጋል። አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የልጅዎ አስተማሪዎች ተጨማሪ ድጋፍ ወይም የበለጠ ፈታኝ ስራ ለማቅረብ ይህንን መረጃ ሊጠቀሙበት ይችላሉ። ይህንን መረጃ በቤት ውስጥ የመማር ጊዜን ለማተኮር ሊጠቀሙበትም ይችላሉ።

የምዘና ውጤቶች የልጅዎን አጠቃላይ የትምህርት ታሪክ እንደማይናገሩ እናውቃለን። በጠቅላላው የልጅዎን የትምህርት ቤት እድገት ሙሉ ምስል የሚፈጥሩ የዘገባ ካርድ ውጤቶችን፣ የክፍል ውስጥ አፈፃፀምን እና የአስተማሪ ግብረመልስን ጨምሮ፣ ውጤቶቹ ከበርካታ ልኬቶች ውስጥ አንዱ ናቸው። በዚያ እይታ ውስጥ፣ አመታዊ ምዘናዎች እርስዎ እና የልጅዎ አስተማሪዎች ባለፈው ዓመት ልጅዎ በግዛት የሳይንስ የይዘት ደረጃዎች ላይ ያሳየውን እድገት በተሻለ ሁኔታ እንዲረዱ ለመርዳት ተዘጋጅተዋል። ምዘናዎች ትምህርት ቤቶች ሁሉንም ተማሪዎች ለመደገፍ ምን አይነት ግብዓቶች እንደሚያስፈልጋቸው በተሻለ ለመረዳት እንድንችል ይረዱናል።

በመጨረሻም፣ ግባችን ተማሪዎች በት/ቤት ስኬታማ እንዲሆኑ እና ህልሞቻቸውን እና ምኞቶቻቸውን ለመከተል ዝግጁ መሆናቸውን ማረጋገጥ ነው። የጠቅላላ ጥያቄዎች ካሉዎት ወይም ስለ ምዘናው ተጨማሪ መረጃ ከፈለጉ፣ እባክዎን በ https://osse.dc.gov/ ድህረ ገፃችንን ይጎብኙ ወይም ከልጅዎ አስተማሪ ጋር ይወያዩ። በተጨማሪም በዚህ መመሪያ ገፅ 4 ላይ ያሉትን ምንጮች በመጠቀም ስለ ምዘናው፣ ስለ ቀጣዩ ትውልድ የሳይንስ ደረጃዎች፣ እና በቤት ውስጥ ጥቅም ላይ ሊውሉ ስለሚችሉ የመማሪያ ግብዓቶች የተሻለ ግንዛቤ ማግኘት ይችላሉ።

በስቴት ትምህርት የበላይ ተቆጣጣሪ ቢሮ (OSSE)፣ ሁሉም ተማሪዎች በከፍተኛ ደረጃ መማር እና ስኬት ላይ መድረስ እንደሚችሉ እናውቃለን፣ በተጨማሪም ልጅዎ ስኬት ላይ እንዲደርስ/እንድትደርስ ከእርስዎ ጋር አብረን የመስራት እድሉን እናደንቃለን።

እናመሰግናለን፣


ዶ/ር Christina Grant
የDC ግዛት የትምህርት የበላይ ተቆጣጣሪ

1050 First Street NE, Washington, DC 20002
(202) 727-6436 TTY: 711 | osse.dc.gov

## የውጤት ዘገባው ሲብራራ፡- ፊት

ይህ መመሪያ ከልጅዎ የውጤት ዘገባ ሊማሯቸው ወደሚችሏቸው በጣም አስፈላጊ የግንዛቤ ነጥቦች ይመራዎታል። እንዲሁም ልጅዎ በቀጣዩ አመት አፈፃፀሙን እንዲያሻሽል ለመርዳት ጠቃሚ ግብዓቶችን ይሰጥዎታል።

---



Science

**Scott Testtaker** — **Grade 8 Science Assessment Results**

Anywhere Middle School — District of Columbia Public Schools

**About This Assessment**

Scott took the DC Science Assessment in Spring 2022. This assessment is designed to assess student achievement of the Next Generation Science Standards (NGSS). These standards ask students to explore three dimensions of science and engineering: scientific ideas, practices, and crosscutting concepts. The DC Science Assessment asks students to engage in three-dimensional tasks that require students to make sense of phenomena and address real-world problems.

These results are one of several ways to understand Scott's needs and strengths. Based on this information, families may work with teachers and schools to identify resources to provide their child support. Schools may use the information in this report to better plan instruction and enrichment for students in the coming school year.

If you have questions about this report, please talk to Scott's teacher or principal or contact District of Columbia Public Schools at (202) 724-4593. If you have questions about the DC Science test, please go to osse.dc.gov/science or contact OSSE at (202) 719-6500.

**How Can You Use This Report?**

This report will help you answer questions about the development of Scott's skills:

- How did Scott score?
- What are Scott's strengths and areas for improvement in this subject?
- How did Scott's score compare to that of other students?

**How Did Scott Perform on This Science Assessment?**

This section shows your student's overall score on the assessment. This overall score determines which performance level your student is in.

**Performance Level**
Level 3
**Score**
459

**Students who score in Level 3**
met expectations
**for middle school science learning standards.**



Level 1 Partially Met Expectations
Level 2 Approached Expectations
Level 3 Met Expectations*
Level 4 Exceeded Expectations*

**Want to know more?**

Turn to the next page to learn about how Scott's results compare to those of other students.

*Levels 3 & 4 indicate that the student has met or exceeded the expectations of the NGSS

### 1) የምዘና መግለጫ


በዘገባው አናት ላይ የምዘናው አጭር መግለጫ አለ። ስለዚህ ዘገባ ማንኛውም አይነት ጥያቄ ካለዎት በአንቀፁ ግርጌ ላይ የአድራሻ መረጃ አለ።

### 2) ልጅዎ በአጠቃላይ አፈፃፀሙ እንዴት ነበረ?

የልጅዎ ውጤት ከአራቱ የአፈፃፀም ደረጃዎች ውስጥ በአንዱ ይመደባል። የአፈፃፀም ደረጃዎቹ ልጅዎ በክፍል ደረጃ የሚጠበቅበትን አሟልቶ እንደሆነ ይለያሉ። በደረጃ 3 ወይም 4 ላይ ያለው ነጥብ ልጅዎ በርዕሰ ጉዳዩ የሚጠበቅበትን አሟልቷል ወይም አልፏል ማለት ነው። ለቀጣዩ የክፍል ደረጃ በሂደት ላይ ነውም ማለት ነው። ከደረጃ 3 በታች የሚያስመዘግቡ ተማሪዎች አሁንም በክፍል ደረጃ ክህሎቶች እና እውቀት እያዳበሩ ሊሆን ይችላል።

## 3) ልጅዎ ምን ያህል የተለየ እውቀት እና ችሎታ ተማረ?

ተማሪዎች ስለ ጥንካሬዎቻቸው እና ተጨማሪ ድጋፍ ሊያስፈልጋቸው የሚችልበት ቦታ ላይ በተለያዩ ክፍሎች የበለጠ ዝርዝር መረጃ ያገኛሉ። ይሄ ክፍል ልጅዎ ለእያንዳንዱ ቁልፍ የምዘና ክፍል የሚጠበቅባቸውን ካሟሉ ወይ ከዛ በላይ ካለፉ፣ ወደ የሚጠበቅባቸው ከቀረቡ፣ ወይ በከፊል የሚጠበቅባቸውን ካሟሉ ተማሪዎች እኩል አፈፃፀም ይኑረው ወይ አይኑረው ያሳያል። የባዮሎጂ ዘገባው ይህንን ክፍል አያካትትም።



Grade 8 Science Details

Performance Level
Level 3

How Did Scott Perform On Key Areas of the Assessment?

…ents who performed at Level 4 overall on this assessment met learning expectations and are likely prepared for the … grade or course. This section shows if your child performed about the same as students who met or exceeded …ctations, approached expectations, or did not yet meet or partially met expectations for each key part of the …essment.

| Physical Sciences | Life Sciences | Earth and Space Sciences |
|---|---|---|
| Expectations using Physical Science principles, skills, and behaviors to make sense of phenomena and address real-world problems | Expectations using Life Science principles, skills, and behaviors to make sense of phenomena and address real-world problems | Expectations using Earth and Space Science principles, skills, and behaviors to make sense of phenomena and address real-world problems |
| Meets or Exceeds ✓ | Meets or Exceeds ✓ | Nearly Meets • |

…r Exceeded Expectations • Approached Expectations – Partially Met Expectations

How Did Scott's Performance Compare?

Scott scored better than 90% of students in Anywhere Middle School who took the Grade 8 Science test. 90%

Scott scored better than 95% of students in District of Columbia Public Schools who took the Grade 8 Science test. 95%

Scott scored better than 88% of students in DC who took the Grade 8 Science test. 88%

0 20 40 60 80 100

…hat Is Next?

…his report to your next conference with your student's …r. You can ask Scott's teachers:

- …hat is Scott learning in science this year?
- How is Scott doing?
- How can I use this information to work with Scott this year?
- What resources should I use to support Scott?

Where Can You Find More Information?

- How Scott's school and other schools scored:
  Call District of Columbia Public Schools at (202) 724-4593
- How the test is designed and what it measures:
  Visit www.OSSE.dc.gov/science or call OSSE at (202) 719-6500
- How families, educators, and schools use these reports:
  Visit www.OSSE.dc.gov/science or call OSSE at (202) 719-6500
- Learn more about what your student will be learning in science:
  Visit www.nextgenscience.org/parentguides

## 4) ልጅዎ ከሌሎች ተማሪዎች ጋር ሲወዳደር እንዴት አይነት አፈፃፀም አሳይቷል?

ይህ ዘገባ የልጅዎ አፈፃፀም ከእሱ በትምህርት ቤት ደረጃ፣ በአካባቢ የትምህርት ኤጀንሲ ደረጃ እና በወረዳው ውስጥ ካሉ እኩዮቹ ጋር እንዴት እንደሚዛመድ ያሳያል።

## 5) ቀጥሎ ምን አለ?

በውጤት ዘገባ ውስጥ ያለው መረጃ የተማሪን አፈፃፀም ለመለካት እና ለክህሎት ግንባታ መመሪያ ለመስጠት የተዘጋጀ ነው። ይህ ክፍል የልጅዎን አስተማሪ ስለ አፈፃፀሙ ሊጠይቋቸው የሚችሏቸውን ጥቂት ጥያቄዎችን ያቀርባል። ተጨማሪ መረጃ የት ማግኘት እንደሚችሉም ያካፍላል።

# ግብዓቶች እና ድጋፍ

ከዚህ በታች የእርስዎ ልጅ አፈፃፀሙን እንዲያሳድግ የሚያግዙ፣ እንዲሁም የውጤት ዘገባን ከልጅዎ እና ከልጅዎ አስተማሪ ጋር ለመወያየት ጠቃሚ ምክሮች የሚሰጡ በርካታ አጋዥ ግብአቶች አሉ።

## ስለ ሳይንስ ውጤቶች ወይም የDC የሳይንስ ምዘና የበለጠ ማወቅ ይፈልጋሉ?

ስለ ተለዋዋጭ የመማሪያ ካርታዎች (DLM) የሳይንስ ምዘና እና የቀጣይ ትውልድ የሳይንስ ደረጃዎች (NGSS) የበለጠ መረጃ ለማግኘት የሚከተሉትን ድህረ ገፆች ይጎብኙ፡

- OSSE.DC.gov/science በውጤት ሪፖርቶች፣ የDC ሳይንስ ምዘና፣ ውጤቶች እና መገልገያዎች ላይ መረጃ ለማግኘት።
- Nextgenscience.org ስለ NGSS የበለጠ ለማወቅ
- nsta.org/parent-q ለግብአቶች እና ስለ NGSS በተደጋጋሚ ለሚጠየቁ ጥያቄዎች።
- DC.mypearsonsupport.com ለ5ኛ እና 8ኛ ክፍል ተማሪዎች የተግባር ፈተናዎችን፣ እና የሁለተኛ ደረጃ የባዮሎጂ ትምህርት ይሰጣል።

## አሁን የልጅዎ የፈተና ውጤቶች ስላሎት፣ ቀጣዩስ ምንድን ነው?

እነዚህን ምዘናዎች ልጅዎን በአካዳሚ ለመደገፍ እንዲጠቀሙባቸው የሚያግዙዎ ብዙ ግብአቶች አሉ። እነዚህ ግብአቶች ተማሪዎችን እና ቤተሰቦችን የመርዳት ብቸኛ ዓላማ ያላቸው አጋዥ መሳሪያዎች እንዲሆኑ የታሰቡ ናቸው። OSSE እና ዲስትሪክቱ እንዚህን የመሰሉ የትኛውም ዓይነት ግብአቶች አይደግፉም እና/ወይም ስፖንሰር አያደርጉም እና እነዚህ መረጃ ሰጪ ምክሮች እንዲሆኑ የታሰቡ ናቸው፥

- NSTA.org/science-resources-parents ለወላጆች የNGSS ትምህርትን የሚደግፉ ግብአቶችን ይሰጣል።
- Exploratorium.edu/snacks/ የተለመዱ፣ ውድ ያልሆኑ፣ በቀላሉ ሊገኙ የሚችሉ ቁሳቁሶችን ተጠቅመው መመራመር እንደሚችሉ ለተማሪዎች የተፈጥሮዊ ክስተት ሳይንሳዊ ምርመራዎችን ያስተዋውቃል።
- HowToSmile.org ለቤተሰቦች በቀላሉ መከታተል የሚችሏቸውን ሳይንሳዊ ምርመራዎች የሚያቀርብ የUniversity of California፣ የBerkeley's Lawrence Hall of Science እና የNational Science Foundation ፕሮጀክት ነው።

## ከልጅዎ ጋር ስለ ውጤቱ ለመነጋገር ይፈልጋሉ?

እንክብካቤ ሰጪዎች ከልጆቻቸው ጋር መነጋገር ላይ ባለሙያዎች ናቸው። ስለልጅዎ የፈተና ውጤት ሲናገሩ ማስታወስ ያለብዎት ጥቂት ጠቃሚ ነገሮች ከዚህ በታች አሉ፡-

- የፈተና ውጤቶች አንድ የአፈፃፀም መለኪያ ብቻ ናቸው።
- ጥንካሬዎች ላይ አተኩሩ።
- የዕድገት ቦታዎችን (ለምሳሌ፣ የኦንላይን ላይ ልምምድ፣ ከአስተማሪ ጋር መስራት) ለመፍታት ስልቶችን ተወያዩ።

## ከልጅዎ አስተማሪ ጋር ስለ ውጤቱ ለመነጋገር ይፈልጋሉ?

ከልጅዎ አስተማሪ ጋር ውይይትን ለመምራት የሚረዱ ጥቂት ጥያቄዎች ከዚህ በታች አሉ፡-

- በዚህ አመት ልጄ በሳይንስ ላይ የመማር ግቦች ምንድን ናቸው?
- ልጄ በሳይንስ ክፍል ውስጥ እንዴት እየሰራ ነው?
- እነዚህን ግቦች ለማሳካት ልጄ በትምህርት ቤት እና በቤት ውስጥ ምን ተጨማሪ ድጋፍ ያስፈልገዋል?
- በእርስዎ ምልከታ ላይ በመመስረት፣ ልጄ በደምብ የሚሰራው ምንድን ነው? ለልጄ አንዳንድ የእድገት ዘርፎች ምንድን ናቸው?